7 DISC INSERT

# መንፈሳዊ ሰው

መንፈሳዊ ሰው ማን ነው? ስራው ምንድን ነው? መንፈሳዊ ሰዎች በምን ይታወቃሉ? እነዚህንና የመሳሰሉት ጥያቄዎች ሁሉ ለአንድ ክርስቲያን መልስ ሊያገኙ የሚገባቸው ናቸው:: በክርስትና ሕይወቴና በአገልግሎቴ ውስጥ ታላቅ ለውጥ ካመጡልኝ መንፈሳዊ እውቀቶች መካከል አንዱ ይሄ ነው:: በዘፍጥረት 2:7 እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው ከምድር አፈር አበጀው፤ይህም ፍጥረታዊን ዓለም እዲገናኝበት ያደረገው ሲሆን በአፍንጫው ደግሞ የሕይወት እስትንፋስ እፍ አለበት:: ያን ጊዜ ሰው ከአምላኩ በተቀበለው መንፈስ አማካኝነት መንፈሳዊውን ዓለም ለመገናኘት ቻለ:: ሰው ከአምላኩ የተቀበለው እስትንፋስ የሰው መንፈስ የሚባለው ነው:: ከምድር አፈር የተሰራው ጭቃ የሆነው የሰው አካልና የእግዚአብሔር እስትንፋስ በሰው ውስጥ ሲገባ ሰው ሕያው ነፍስ ያለው ፍጥረት ሆነ:: ይህ የሰው ነፍስ ነው:: የሰው ነፍስ ሰው ራሱንና አካባቢውን እንዲለይ አድርጎታል::



ታዲያ አንድ ክርስትያን አፈጣጠሩን ለይቶ ሲረዳና በየትኛው ክፍሉ ምን ማድረግ እንዳለበት ሲያውቅ በምድር ላይ የተፈጠረበትን ዓላማ አውቆ ለመኖር በሚያደርገው የሕይወት ጎዳናው ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማደረጉ ግልጽ ነው:: በዚህ አልበም ውስጥ ሰፋ ባለ መልኩ የሰው ፍጥረታዊ አካል ነፍሱንና መንፈሱን ምን እንደሆኑ፣ ሥራቸው ምን እንደሆነ፣ እንዴት እንደምንለያቸውና እንዴት እንደምንጠቀምባቸው በግልጽ ተብራርቶ ተቀምጦአል::

ይህ መልዕክት ለእርስዎና ለቤተሰብዎ እንዲሁም ለሚያውቋቸው ሁሉ ታላቅ የመንፈሳዊ ሕይወት እድገት የሚያመጣ ስለሆነ ረጋ ብለው ቢያዳምጡትና ደጋግመው ቢሰሙት እንደሚጠቀሙበት የጌታም መንፈስ የቃሉን ፍቺ እንደሚያበራልዎ በመተማመን ምንም ዓይነት ጥያቄና አስተያየት ቢኖርዎት በስልክ ቁጥር (651) 772-0216 ወይንም በአድራሻችን ቢጽፉልን ይደርሰናል::

ሚኔሶታ በምትገኘው የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን ዋና መጋቢ

መጋቢ እንድርያስ ሐዋዝ 2009

አድራሻችን
Ethiopian Evangelical Church In Minnesota ◆ 770 7th st. East ◆ St.Paul, MN 55106
(651) 772 0216 ◆ www.eecmn.org

መንፈሳዊ ሰው

በፓስተር እንድርያስ ሐዋዝ

# መንፈሳዊ ሰው



በፓስተር እንድርያስ ሐዋዝ
7 CDs